# አምላካችንን ማወቅ

ማነው የፈጠራችሁ?

ማነው የፀጉራችሁን እና የአይናችሁን ከለር የሰጣችሁ?

ማነው ርዝመታችሁ ምን ያህል እንደሚሆን እና የቆዳችሁ ከለር ምን አይነት መሆን እንዳለበት የወሰነው?

ማነው እናታችሁን፣ አባታችሁን እና ጓደኞቻችሁን የፈጠረው?

ተራራዎችን፣ ዛፎችን፣ ባህርን እና ፀሀይን እንዲሁም ጨረቃን የፈጠረው ማነው?

ማነው ድመቶችን እና ውሾችን፣ ሽኮኮዎችን፣ ቀጭኔዎችን እና ሌሎች ፍጥረታትን የፈጠረው?

ሁላችሁም ጥያቄውን በተመሳሳይ መልክ ትመልሳላችሁ "አላህ እነኝህን እና የተቀሩትን ሁሉንም ነገሮች ፈጠረ"፤በርግጥ ይህ ትክክለኛ መልስ ነው፡፡

የእኛ እና የፍጥረተ አለሙ ፈጣሪ የሆነውን ሃያሉ አላህን ምን ያህል ታውቁታላችሁ?

አላህ እራሱን በቁርአን ላይ ገልፆልናል፡፡

በዚህ ፊልም አላህ (ሱ.ወ)ን በቁርአን አንቀፆች በማወቅ ወደ እሱ ለመቅረብ እንሞክራለን፡፡

## አላህ የመጀመሪያ ነው ከሁሉም ነገር በፊት ነበር

**"እርሱ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ግልፅም ስውርም ነው፡፡ ሁሉንም ነገር አዋቂም ነው፡፡" (ሱረቱል ሐዲድ ፡3)**

የምንኖርባት አለማችን የግዙፉ ፍጥረት አለም አካል ናት፡፡

በታሪክ ውስጥ ሰዎች ይህ ግዙፍ ፍጥረት አለም መጀመሪያ ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም የሚለው ነገር እጅጉኑ ያስገርማቸው ነበር፡፡ በ ሀያኛው ክፍለ ዘመን ፍጥረተ አለሙ መጀመሪያ እንዳለው ተረጋገጠ፡፡

በ1929 ኤድዊን ኸብል የሚባል ተመራማሪ ፍጥረተ አለሙ ሁልጊዜ እንደሚለጠጥ ተመለከተ። ከዚህ እውነታ በመነሳት ሳይንቲስቶች አንድ መደምደሚያ ላይ ደረሱ። አንድ ሰው ወደ ኋላ ቢመለስ ፍጥረተ አለሙ እያነሰ ይሄዳል። እናም እያነሰ የሄደው ፍጥረተ አለም በመጨረሻ አንድ ነጥብ ይሆናል። ስለዚህ ፍጥረተ አለሙ የተገኘው ከዚህ ነጥብ ፍንዳታ ነው።

ነገር ግን እዚህ ጋር ትልቅ ሚስጥር አለ።ፍንዳታዎች አካባቢያቸው ያለውን ነገር ያበላሻሉ። የዚህ ምሳሌ የእሳተ ጎሞራ ፍንዳታ ነው። የዚህ አይነት ፍንዳታዎች አካባቢው ላይ የሚገኙ ነገሮችን በሙሉ ያጠፋሉ። ቤቶችን በማፈራረስ ዛፎችን ይነቅላሉ።

ፍጥረተ አለሙን የፈጠረው ፍንዳታ ከቢሊዮን የእሳተ ጎሞራ ፍንዳታዎች ይበልጥ ነበር።

ነገር ግን ከሌሎች ፍንዳታዎች በተፃራሪ ይህ ፍንዳታ ፍጥረተ አለሙን ፍፁም በሆነ ስርአት ገነባው።

ይህ የሚያሳየው ገደብ የሌለው ኃይል ያለው ፈጣሪ እንዳቀናጀው ነው። ይህ ገደብ የለሽ ኃይል ያለው ፈጣሪ አላህ (ሱ.ወ) ነው።

አላህ(ሱ.ወ) ፍጥረተ አለሙን የሰራ ፍንዳታን በመፍጠር በዚህ ፍንዳታም ፍፁም የሆነ ስርአትን ገነባበት።

ፍጥረታት፣ ኘላኔቶች እና ፍጥረተ አለሙ ከመፈጠራቸው በፊት አላህ ብቻ ነበር። እሱ የመጀመሪያው ነው።

## አላህ የምንሰራቸውን ስህተቶች ይምራል

**“መልካም ስራን ግልፅ ብታደርጉ ወይም ብትደብቁ ክፉ አድራጎትንም ይቅር ብትሉ አላህ ይቅር ባይ ሀያል ነው።” (ሱረቱል አኒሳእ:149)**

ከጊዜ ወደ ጊዜ ሁላችንም ስህተት እንሰራለን፣፣ የአንድ ነገር ገፅታዎችን በሙሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት አቅቶን የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ልንደርስ እንችላለን። አግባብ ያልሆነ ፀባይም ልናሳይ እንችላለን። ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) ስለፈጠረን ድክመታችንን አውቆ ስህተታችንን ይቅር ይለናል። እኛም ስህተታችንን በመለየት እና በመፀፀት በድጋሚ ላለመስራት መወሰን ይኖርብናል። አላህ እንዲምረንም ዱዐ ማድረግ ይኖርብናል።

ይህን የምናደርገው ከልብ ከሆነ አላህ ስህተታችንን በማመር ምህረት ያደርግልናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ላይ ከልብ ወደ እሱ መመለስ ስላለው ጥቅም ይነግረናል፡፡

**"አላህ የሚቀበለው የነዚያን ሐጢዐትን ባለማወቅ የሚሰሩትን እና ወዲያውኑም ንሰሀ የሚገቡትን ሰዎች ንሰሀ ነው፡፡ አላህ የእንዲህ አይነት ሰዎችን ስራ ይቀበላል፡፡ አላህ አዋቂ ጥበበኛ ነውና፡፡" (ሱረቱ ኒሳእ፡17)**

## አላህ ሁሉንም ነገር ያውቃል

**"አላህ የሰማያትንም ሆነ የምድርን ሚስጥሮችንም ሁሉ አዋቂ ነው፡፡ ከልቦች ውስጥ ያሉ ሚስጥሮችንም በሙሉ ያውቃል፡፡" ሱረቱል ፋጢር፡ 38**

አላህ ሁሉንም ነገር ያውቃል፡-

ሰማያት እና ምድርን እንዲሁም በመሀከላቸው ያሉትን ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ ያውቃል፡፡

በያንዳነዱ ቅፅበት ምን እንደሚከሰት ያውቃል፡፡

በየደቂቃው በአለማችን ዙሪያ የሚወለዱት እና የሞቱትን ሰዎች ብዛት ያውቃል፡፡

በአለማችን ላይ ከሚገኙት ዛፎች በሙሉ ምን ያህል ቅጠል አንደሚረግፍ ያውቃል፡፡

በዩኒቨርሱ ውስጥ ለሚገኙት በቢሊዮን የሚቆጠሩ ጋላክሲዎች ውስጥ የሚገኙ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብትን ያውቃል፡፡

በዝርዝር ልንፅፋቸው የሚችሉ ሁሉንም ነገሮች ያውቃል፡፡

ይህን በቁርአን ላይ እንደሚከተለው ገልፆልናል፡፡

**"…በየብስም በባህርም ውስጥ ያሉ ፍጡራንን ሁሉ ያውቃል፡፡ ከቅጠልም ምንም አትረግፍም እርሱ የሚያውቃት ቢሆን እንጂ…" ሱረቱል አንአም፡59**

መርሳት የማይገባን አንድ ነጥብ አለ አላህ በግልፅም ሆነ በድብቅ ምንሰራውን እንዲሁም የምናስበውን ነገር በሙሉ ያውቃል። የሰራነውን ነገር ከሰዎች መደበቅ እንችላለን። ነገር ግን ከአላህ እይታ ውጪ ልናደርገው አንችልም። እውቀቱ ሁሉንም ፍጥረተ አለም ያካበበ ነው።

## አላህ እፁብ ድንቅ ነው

"በሰማያት እና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው። እርሱም በላዩ ታላቁ ነው።" (ሰረቱል ሹራ፡4)

የአላህ የበላይነት ከኛ የመረዳት ችሎታ በላይ ነው። ነገር ግን የፈጠራቸውን ፍጥረታት ስንመለከት የእሱን ታላቅነት መረዳት እንችላለን። ምን ያህል ኃይል እንዳለውም እናያለን።

ብዙ ቶኖችን የሚመዝኑ ደመናዎችን የያዘው ሰማይ።

ወደ ሰማይ በሺዎች የሚቆጠሩ ጫማዎች የሚረዝሙ ተራሮች።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ የተለያዩ ፍጥረታትን የያዙ ባህሮች።

ብዙ እንስሳት የሚኖሩባቸው ደኖች…

እነዚህና ሌሎች ለመቁጠር የሚያዳግቱ ነገሮች ከአላህ ታላቅነት ምልክቶች ውስጥ ናቸው።

## አላህ የፈለገውን ያደርጋል

"አላህ ከርሱ ውጭ ሌላ አምላክ የሌለ የሆነ፣ ንጉስ፣ ከጉድለት ሁሉ የጠራ፣ የሰላም ምንጭ፣ የእምነት የበላይ ጠባቂ፣ ባሮቹን ተቆጣጣሪ፣ አሸናፊ፣ ሐያል እና ኩሩ አምላክ ነው።…" (ሱረቱል ሀሽር፡23)

አካባቢያችን ላይ የተወሰኑ ጉረኛ ሰዎች ይገኛሉ። ከሌሎች የተሻልን ነን ብለው ያስባሉ።ያላቸው ችሎታና ተሰጥኦ የእነሱ ይመስላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ በትእቢት የፈጣሪን ድንበር ይጥሳሉ።

ነገር ግን ይህ የማይረባ አስተሳሰብ ነው። ማንም ሰው ወደዚህች አለም የመጣው ፈልጎ አይደለም። እንዲሁም ሕይወቱ መቼ እንደሚያልፍ አያውቅም። ያለበትን ሁኔታ በምርጫ አይደለም ያገኘው።

አላህ ነው ያለንን ችሎታ እና ተስጥኦ የለገሰን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሰጠንን ነገር በፈለገው ሰዓት መውሰድ ይችላል፡፡ አላህ እፁብ ድንቅ ነው የፈለገውን ያደርጋል፡፡

## አላህ ለሰው ልጆች ፀጋዎችን ይሰጣል

**“አላህ ሲሳይን ለጋሽ፤ የብርቱም ሀይል ባለቤት ነው፡፡” (ሱረቱ አዛሪያት፡58)**

አላህ ወሰን የለሽ ምህረት አለው፡፡ እሱ ለሰጠን ፀጋዎች ምስጋና ይገባቸው እና መኖር ችለናል፡፡

አላህ ከመሬት ውስጥ የሚበቅሉትን ተክሎች ለእኛ ፈጥሮልናል፡፡

እሱ መሬትን ሳናርሳት እንኳን አረንጓዴ ተክሎችን እና የጥራጥሬ ዛላዎችን አብቅሎልናል፡፡

ቢጫ፣ ቀይ፣ አረንጓዴ እና ብርቱካናማ ፍራፍሬዎች እና አትክልቶች ከመሬት ውስጥ ይበቅላሉ፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ከእግራችን በታች መሬት ውስጥ አራት ሺህ አምስት መቶ ዲግሪ ሴልሺየስ ሙቀት ያለው እሳት እንዲኖር አድርጓል፡፡

በቶን የሚመዘን ንፁህ ውሀን ከሰማይ ያዘንባል፡፡

ሰማያዊ ባህሮችን በሺዎች በሚቆጠሩ ፍጥረታት ሞልቶዋቸዋል፡፡

በየቅፅበቱ አላህ (ሱ.ወ) ሳንባችንን የሚሞላውን ኦክስጅን ፈጥሯል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ለእኛ የፈጠረልንን ፀጋዎች ቆጥረን አንዘልቃቸውም፡፡ ይህ እውነታ በቁርአን ላይ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

**“ለሕይወት የሚያስፈልጓችሁንም ነገሮች ሁሉ ሰጥቷችኋል፡፡ የአላህን ፀጋዎች ቆጥራችሁ አትዘልቋቸውም፡፡…” (ሱራ ኢብራሂም፡34)**

አላህ  (ሱ.ወ) እነዚህን ፀጋዎች እንደሰጠን መርሳት የለብንም፡፡ ሁልጊዜ እሱን ማስታወስና ማመስገን ይኖርብናል፡፡

## አላህ (ሱ.ወ) የታመሙ ሰዎችን ያድናል

"ስታመም ፈውስን ይለግሰኛል።" ሱረቱ ሹዐራ፡80

ስንታመም ምን ያህል ደካማ እንደሆንን እና አላህ ምን ያህል እንደሚያስፈልገን እንገነዘባለን።

አላህ ደካማ መሆናችንን ሊያሳውቀን በመቶሺዎች የሚቆጠሩ በሽታዎችን ፈጥሯል።

የሰው ልጅን እጅግ የሚያዳክመው ቫይረስ ወይም አንዳንድ ጊዜ ለመለየት የሚያስቸግረው ወደ ሰውነታችን የገባ ጀርም የአላህ ኃያልነት ግልፅ ምልክቶች ናቸው።

አንድ ቫይረስን ለማጥፋት በተመራማሪዎች የተደረጉ ጥናቶች እና ሙከራዎች የአላህ የመፈጠር ጥበብ የበላይነትን ያሳያሉ።

ምክንያቱም አላህ ነው ሕመምን የፈጠረው። ሕመሙም ሊወገድ የሚችለው እሱ ሲፈልግ ብቻ ነው። እንደ አዳኝነቱ እሱ ከፈለገ ያመጣውን በሽታ ያነሳዋል።

የእሱ ፍላጎት ካልሆነ በአለም ላይ የሚገኙ ዶክተሮች እጅግ ከረቀቁ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎቻቸው እና መድሀኒቶቻቸው ጋር ሰወዬውን እንዲሻለው ማድረግ አይችሉም።

ሁሉም መድሀኒቶች ሕመምን የማዳኛ ሰበቦች ናቸው። አላህ ከፈለገ የታመመው ሰው በሕክምና እንዲድን ያደርጋል። እሱ ሕመምተኛው እንዲድን ካልፈለገ ቀላል በሽታ እንኳን የሰውዬውን ሞት ሊያመጣ ይችላል።

ስለዚህ እኛ ማድረግ ያለብን የአላህን ገደብ የለሽ ሀይል በማስታወስ ስንታመም ዱዐ ማድረግ ነው።

## በድጋሚ እናስተንትን

አላህ (ሱ.ወ) ፈጥሮን ሲያበቃ በርካታ የተለያዩ ፀጋዎችን ሰጥቶናል።

ኃይሉ ከሁሉም ነገር በላይ ነው።

በውስጣችን ያሰብነውን እና የምንሰራውን ነገር በሙሉ ያውቃል።

የሰራነውን ስህተት ይምረናል፡፡

ስንታመም ያድነናል፡፡

ማድረግ የሚገባን ነገር አላህን በደንብ በማወቅ ትእዛዙን ማክበር ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ላይ ይህን ገልጿል፡፡

**“በሰማያት እና በምድርም ውስጥ ያሉ ሁሉ የአላህን ክብር እና ልእልና መሠከሩ፡፡ እርሱ ሐያል እና ጥበበኛ ነው፡፡ የሰማትም የምድርም ንግስና የርሱ ብቻ ነው፡፡ ሕይወትን ይለግሳል፡፡ ይነፍጋልም፡፡ እርሱ ሁሉንም ነገር ቻይ ነው፡፡ እርሱ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ግልፅም ስውርም ነው፡፡ ሁሉንም ነገር አዋቂም ነው፡፡” (ሱረቱል ሐዲድ፡1-3)**